| | |
|---|---|
| ዐይነት ፲ | መሥራች ፡ ጽሑፍ ። |
| ርእስ ፲ | "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡— ሥልጡንሕዝብና ። ሥልጡንሕዝብና ፥ የአቢሳን ፡ ቤዛ ። " |
| ደራሲ ፲ | ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ። |
| ዕለት ፲ | ጥር ፡ 1986 ። |
| ዝግጅት ፲ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፲ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ 2011.003 ። |
| ማስታወሻ ፲ | ከ 23 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ በድጋሚ ፡ የወጣ ። |
| ማሳሰቢያ ፲ | |


# መሥራች ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur | مَقالة تاسيسى

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡— ሥልጡንሕዝብና ።

## ሥልጡንሕዝብና ፥ የአቢሳን ፡ ቤዛ ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

[ሥልጡንሕዝብና ፥ ፋ ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.007 ፥ ጥር ፡ 1986 ፡ ዓ.ም. ።]

ቀጥሎም ፥ በየዘመኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተከሥቶ ፣ ጐልቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በምናገኘው ፡ ድርሱ ፡ እንደምንረዳው ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ ለአቢሳን ፥ የሕዝብነታቸው ፡ ዐብሮ ፡ በቀል ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፥ ከውስጥ ፡ የተነሣ ፡ ዐማጺን ፡ ሲዳኙበት ፥ ከውጭ ፡ የመጣ ፡ ጠላትን ፡ ሲመክሩበትና ፥ ጊዜን ፡ ለመከተል ፥ ዐጻራቸውን ፡ ሲያዘምኑበት ፡ ዐብሯቸው ፡ ሊኖር ፡ ነው ።

ይህውም ፡ ሊታመን ፥ ሕዝብ ፡ አቢስ ፡ በነገሥተ ፡ አቢሳን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ በነጻነትና ፡ በሰላም ፡ ዘንተው ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፥ የቅንጦታቸው ፡ ብዛት ፡ ከባድ ፡ ቅልጣንን ፡ አምጥቶባቸው ፥ አንድ ፡ የሚያደርጋቸውን ፡ አንዱን ፡ ፈጣሪ ፡ አምላካቸውን ፡ ክደው ፥ በብዙው ፡ ፍጡሩ ፡ (ማለት ፥ በሰማዩ ፣ ምድሩ ፣ ባሕሩ ፣ ደፈሩ ፣ ዘንዶው ፣ እባቡ) ፡ አምልኮት ፡ ተለያይተው ፥ "ለየብቻችን ፡ እንደር" ፡ በማለት ፥ የማትከፋፈለውን ፡ አገራቸውን ፡ "እንከፋፍል" ፡ ሲሉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጣልተው ፥ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ሲተላለቁ ፥ ከቶ ፡ የሚያድናቸው ፡ አንዳች ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ሥልጣን ፡ አልተገኘም ፡ ነበር ።

ፍንጭ ፡ በሌለው ፡ ጦርነት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጨራርሰው ፥ ከመጠን ፡ አንሰው ፥ በግብር ፡ ታጥተው ፥ በነገድነት ፡ ሲጠፉ ፥ ርዝራዣቸው ፡ ጦር ፡ ለማንሣትና ፡ ግንባር ፡ ለመሥራት ፡ ለቻሉት ፡ ነገዶች ፥ አቢስ ፣ በለው ፣ ሳባ ፣ ኖባ ፥ እንደያቀረባቸው ፡ በምንዝርነት ፡ (ተዳባይነት) ፡ ዐደሩ ። ይህውም ፡ ለኹሉም ፡ በጃቸው ። ከሽማግሌዎቻቸው ፡ ይልቅ ፡ መከራው ፡ መከራቸው ። ጦርነት ፡ ከሚፈጁቸው ፡ በፊት ፥ እንርሱ ፡ ጦርነቱን ፡ ፈጁት ። በመብትና ፡ በግዴታ ፡ በማስተካከል ፡ አፋቅሮ ፡ በሰላም ፡ ያስተዳድረናል ፡ የሚሉት ፡ ከኹላቸው ፡ እኩል ፡ የሚወለድና ፡ በኹላቸው ፡ እኩል ፡ የሚወደድ ፡ ሰው ፡ ከመኻከላቸው ፡ ቢያጡ ፥ ለኹላቸው ፡ እኩል ፡ ባዕድ ፡ የኾነውን ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ኹላቸውም ፡ እኩል ፡ ፈርተው ፡ የሚያመልኩትን ፡ አርዌን ፡ ለማንገሥ ፡ ተስማሙ ። በስምምነታቸውም ፡ አንድነታቸውን ፡ እንደገና ፡ አጸኑ ። ባንድነታቸውም ፡ እግዚእናቸውን ፡ ተጐናጸፉ ። ክሂላቸው ፡ ሞልቶላቸው ፥ አርዌን ፡ በፈቃዳቸው ፡ አንግሠው ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥታቸውን ፡ መልሰው ፡ አቁመን ፥ በሰላምና ፡ በፍትሕ ፡ ዐደሩ ።

ሕዝብ ፡ አቢስ ፥ በዚህ ፡ ድንቅ ፡ ድርስ ፥ የግለኛ ፡ ብጤን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ መሳው ፡ ተወላጁ ፡ ሲተባበር ፥ ከተፈጥሮ ፡ የታደለውን ፥ የራሱ ፡ ጌታ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰብኣዊ ፡ መብት ፡ አስከብሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚያስችለው ፡ ካንድነቱ ፡ ሲሰፍንለት ፥ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ሕዝባዊ ፡ እግዚእናው ፡ ካንድነቱ ፡ ሲሠርጽለት ፡ ተመልክቷል ። ሞላው ፡ ተወላጁ ፡ ሲተባበር ፥ ካንድነቱ ፡ የሚሠጽርው ፡ እግዚእናም ፥ ተወላጁ ፡ ሲበታተን ፡ ከመኻከሉ ፡ የሚጠፋና ፥ ባዶው ፡ ሞላውን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚያጣፋ ፡ የችሎት ፡ ሕጸጽ ፣ ፍጹም ፡ ስእነት ፣ ወይም ፡ የቅዱስ ፡ ፍላጎት ፡ ዕጦት ፣ ምቀኝነት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝቦ ፥ ድኅነቱ ፡ በየግንባሩ ፡ እኩል ፡ የግለኛውም ፡ የማኅበሩም ፡ ገንዘብ ፡ የኾነው ፡ እግዚእናው ፡ መኾኑን ፡ ዐውቋል ። እግዚእናውም ፡ ከባለቤቱ ፡ አንድነቱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ሊያሠርጸው ፡ የማይቻለው ፣ የማይገባው ፣


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ያልታደለው ፡ ዕርሙ ፡ ሲኾን ፥ አንድነቱ ፡ ግን ፥ ለፈቀደው ፣ በፈቀደው ፣ እንደፈቀደው ፡ ሊያውለው ፡ የተገባው ፤ ሲሻውም ፡ ስንኳን ፡ ለራሱ ፣ ለመሰሉ ፡ ለሰው ፥ ላውሬው ፡ እንኳ ፡ ቢሰጠው ፥ ተቈጭ ፣ ቈራጭ ፣ ፈላጭ ፡ የሌለበት ፥ የፈለገውን ፡ ጕዳይ ፡ የሚፈጽምበትና ፡ የተመኘውን ፡ ውጤት ፡ የሚያገኝበት ፥ ከባሕርዩ ፡ ያሠረጸው ፡ ጌትነቱ ፥ የማይዳሰስ ፣ የማይገሰስ ፡ ሥልጣኑ ፡ መኾኑን ፡ በደረሰበት ፣ ባየውና ፡ ባደረገውም ፡ ተረድቶ ፥ ተከታይ ፡ ትውልዱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዘለቄታው ፡ ያስረዳ ፡ ይመስላል ፡፡ እንሆ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናየው ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ ለመቼውም ፡ ሊኖር ፡ ነው ፡፡

በውኑ ፥ ያርዌ ፡ መንግሥት ፥ መላው ፡ አቢሳን ፡ የወደደው ፥ ልጁ ፡ የሚሠዋለት ፡ ምልክና ፡ ነበር ፡፡ ግዛቱም ፥ ሐጋጊውን ፣ ፈጻሚውንና ፡ ፈታሒውን ፡ ሥልጣን ፡ ያዋሐደ ፡ ችሎት ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፥ መላኪዎቹ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፥ እየቈየ ፡ አድሎኛ ፡ ኾነ ፤ ግፍን ፡ አዘወተረ ፡፡ ግፉም ፥ ከታች ፡ ከደካማው ፡ አንሥቶ ፥ እያደር ፡ ወደ ላይ ፣ ወደ ፡ ኀያላኑ ፡ እየተረማመደ ፡ ወጥቶ ፥ ኹሉን ፡ እኩል ፡ የሚያጠፋቸው ፡ መኾኑ ፡ ለኹሉም ፡ እኩል ፡ ሲሰማቸው ፥ የጭንቃቸው ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ አንድ ፡ አድርጓቸው ፥ የወል ፡ ዠግናቸውን ፡ አጋቦስን ፡ ጠርተው ፥ "አርዌን ፡ ገድለኽ ፡ ከቀንበሩ ፡ ነጻ ፡ ያወጣኸን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እናንግሥኻለን ፡፡ እኛ ፡ ላንተ ፣ ልጆቻችን ፡ ለልጆችኽ ፡ ታማኝ ፡ ዜጎች ፡ ኾነን ፥ ዐልጋኽን ፡ ከዘርኽ ፡ ሳናወጣ ፡ እንኖራለን" ፡ ብለው ፥ የታወቀውን ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ አሰሩ ፡ ድረስ ፥ ከቀንበሩ ፡ ነጻ ፡ የሚያወጣቸው ፡ አንዳች ፡ ታዳጊ ፡ አላገኙም ፡ ነበር ፡፡ እንዳሰሩ ፡ ግን ፥ አንድነታቸውን ፡ አገኙ ፤ ሥልጡንሕዝባዊው ፡ ክሂል ፡ ሞላላቸው ፡፡ ባንዱ ፡ ዠግናቸው ፡ ዐብረው ፡ ኼደው ፥ አርዌን ፡ ገድለው ፥ የፍትሕ ፡ መንግሥታቸውን ፡ እንደገና ፡ በርትዕ ፡ ሠሩ ፤ ርሱም ፡ በሙብትና ፡ በግዴታ ፡ ተመዛዛኝነት ፡ በረጋ ፡ ዛኀን ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ሊኖር ፡ ነው ፡፡

አቢሳን ፥ ሥልጡንሕዝብናን ፡ ያናዎሩ ፡ መነሻ ፣ መገሥገሻና ፡ መድረሻ ፡ አድርጎ ፡ ሲሠራ ፥ አንድነቱን ፡ እያጠነከረ ፡ ችሎቱን ፡ አዳበረ ፡፡ ያገርን ፡ ሥራ ፡ የኀብረት ፡ በሚያደርግበት ፡ አገባብ ፡ የግለኛ ፡ አባሉም ፡ እያደረገ ፡ ክንዋኔውን ፡ ተከፋፍሎ ፡ አገመረው ፡፡ የብጤዎቹን ፡ አህጉራት ፡ ሙብትና ፡ ነጻነት ፡ በግራም ፡ በቀኝም ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ እያከበረም ፥ ብድሩን ፥ ርሱ ፡ በብጤዎቹ ፡ ተከበረ ፡፡ ከዚህም ፡ በላይ ፥ በተፈጥሮ ፡ የታደላትና ፡ የህላዌው ፡ ያዋሐዳት ፡ ያፍሪቃ ፡ ቀርን ፡ ብሔሩ ፥ ዙሪያዋን ፡ በውሃ ፡ የተቀጠረች ፣ በእሳት ፡ የታጠረችና ፡ በያፋፉ ፡ በቃጥላ ፡ የታቀበች ፡ ምጥቅት ፡ ተራራ ፡ መኾኗ ፥ ማንኛውንም ፡ ዐመፀኛ ፡ ለወረራ ፡ ወይም ፡ ለዘረፋ ፡ ተስፋ ፡ ሲያስቈርጥ ፥ ገነቷ ፣ ሀብቷና ፡ አየሯ ፡ ደግሞ ፥ በፍቅር ፡ ለመግባት ፡ ያያትንና ፡ በዝናዋ ፡ ያወቃትን ፡ ኹሉ ፡ አጐመዠ ፡፡

በ፫ ፡ ሺሕ ፡ ፺፱ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ግድም ፥ በሴም ፡ ልሳነ ፡ የብስ ፡ የተነሣው ፡ የሰባቱ ፡ ዓመት ፡ ረኃብ ፡ ሰውን ፡ በፈጀ ፡ ጊዜ ፥ አንጋደ ፡ ሴም ፣ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፣ ነገደ ፡ ኀምያር ፣ ነገደ ፡ ሐበሻት ፡ እያሠኑ ፥ ጓዝ ፡ ጕዝጓዛቸውን ፡ ይዘው ፥ ከደቡብ ፡ የመን ፡ ተነሥተው ፥ እንዳንበጣ ፡ በዝተው ፥ በመከራው ፡ በር ፡ በባብ ፡ ኤልመንደብና ፡ በዐጸባው ፡ መልካ በዐሰብ ፡ በኩል ፡ አቢስያ ፡ ገቡ ፡፡ ቀጥሎም ፥ እስራኤላውያን ፡ ከምስር ፡ ሲወጡ ፥ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ አስቀድመው ፡ ለርዳታ ፡ ምስር ፡ ኼደው ፡ ከነበሩት ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ የሚኾኑ ፡ የአበሳንያ ፡ ዐርበኞች ፡ ጋራ ፥ መጠናቸው ፡ የበዛ ፡ ካማት ፡ (ቅማንት) ፡ አባይን ፡ ተከትለው ፡ መጥተው ፡ አበሳንያ ፡ ገቡም ፥ ተሰደዱም ፡፡

አቢሳን ፥ ኹሉንም ፡ በየጊዜያቸው ፥ በሰላምና ፡ በርኅራኄ ፡ እየተቀበለ ፥ በሙብትና ፡ በግዴታ ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ ባገሬነት ፡ አስተካክሎ ፥ በሥልጡንሕዝብና ፡ ሲሠራ ፥ አንድንም ፡ አገር ፡ ሳያጠቃ ፣ ባንድ ፡ አገር ፡ ሳይጠቃ ፡ ኖረ ፡፡

ከዚያም ፥ አጋቦሳዊው ፡ ዘርዐ ፡ ንጉሥ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ ፸፫ ፡ ነገሥታትን ፡ አከታትሎ ፥ እ፸፬ኛው ፡ ተራ ፡ ላይ ፥ ማክተሚያው ፡ እኾነችው ፡ ስመ ፡ ጥሯ ፡ ማክዳ ፣ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ወሳባ ፡ ንግሥ ፡ ድረስ ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ በሰላምና ፡ በፍትሕ ፡ እየሠራ ፡ መጣ ፡፡

*(ይቀጥላል ፡፡)*


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡